
# እ.ኤ.አ ከማርች 1-10/2019 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የምዕራብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ዳርቻ አካባቢዎች ላይ ፀሃያማ እና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ነበር የተስተዋለዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በተጠቀሱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በሌላ በኩል ዝናብ ሰጪ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገፅታ ነበራቸዉ፡፡ በዚሁ መሰረት የበልግ አብቃይ የሆኑ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን አልፎ አልፎ ከነበራቸዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በጥቂት ስፍራዎቻቸዉ ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ በጅማ፣ በምስራቅ፣ ወለጋ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በወላይታ እና ጋሞ ጎፋ ዞኖች ላይ ከ25-105 ሚ.ሜ ከ4-8 ለሚደርሱ ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በፋፈን፣ በመስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በአርሲ እና ባሌ፣ በኢሉአባቦራ፣ በጥቂት የጉጂ እና ቦረና ዞኖች፣ በሰገን ህዝቦች፣ በቤንች ማጂ፣ በደቡብ ጎንደር፣ በአፋር ክልል ዞን 03 እና 05 ላይ ከ5-25 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-4 ቀናት ያህል ዝናብ ዘንቧል(ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በሰሜን ሸዋ(04)፣ በምስራቅ ሸዋ፣ በምዕራብ ሸዋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ፣ ወለጋ፣ በምስራቅ ሀረርጌ፣ በፋፈን፣ በሰገን ህዝቦች፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በወላይታ እና ጋሞ ጎፋ፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜን ሸዋ(03)፣ በምዕራብ ትግራይ፣ በሰሜን ጎንደር፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ።


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10 /2019 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




## **እ.ኤ.አ ከማርች 1- 10/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ**

## **በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ**

ባሳለፍነዉ የማርች ወር የመጀመሪዉ አስር ቀናት በአብዛኛው የበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ቀድመዉ ለተዘሩ የበልግ ሰብሎችና ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ እንዲሁም ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ገንቢ ሚና የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የማሳ ዝግጅት ለማድረግ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረዉ፡፡ በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀ፣ ለግጦሽ ሳር አቅርቦትና ለቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው። በሌላ በኩል የእርጥበት እጥረት በሚኖርባቸዉ አካባቢዎች አልፎ አልፎ የተገኘውን እርጥበት በማሳቸው ላይ በማቆየት ለሚጠቀሙት አካባቢዎች ጥሩ አጋጣሚ እንደነበረው ይታመናል (ካርታ 4)።


ካርታ 4፡ እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# <u>እ.ኤ.አ ከማርች 1-10/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>ውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ 1-10 ማርች 2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን የተስተዋለባቸው ተፋሰሶች ጥቂት የላይኛዉ እና የመካከለኛው አዋሽ፣ የአባይ ደቡባዊና ምስራቃዊው ክፍል፣ የላይኛዉና መካከለኛዉ ባሮ አኮቦና ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የላይኛዉ ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም የላይኛው ተከዜ አካፋይ የሆኑት ከፍተኛ ኪስ ቦታዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በጥቂት ምዕራባዊ ባሮአኮቦ፣ የታችኛዉ ኦሞጊቤ እና ስምጥሸለቆ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከፊል ደረቅ ሁኔታ ከመስተዋሉ በስተቀር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ያመዘነ ነበር (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5፡ እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2019 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# <u>እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2019 የሚኖረው</u>

# <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች አጋማሽ በኋላ የወቅቱ ዝናብ አብዛኛውን የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን በማካተት የሚዘንብ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ ያገኛሉ።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መኖር መንስኤ የሚሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚሁ ጋር ተያይዞ<u>ም</u> በአንዳንድ የበልግ ዝናብ አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖርና በጥቂት ቦታዎችም ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም ይችላል።

በአጠቃላይ በመጪው አሥር ቀናት <u>ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ እና ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ አርሲና ባሌ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሀረርጌ፣ ቦረናና ጉጂ ፣አዲስ አበባ፣ የጋምቤላ ክልል አንድ፣ ሁለት እና አራት ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ የካማሺ ዞን፣ ከትግራይ የደቡብ እና የምሥራቅ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ዋግ ህምራ፣ ባህር ዳር እንዲሁም ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም ዞኖች በተጨማሪም ጥቂት የደቡብና የሰሜን ጎንደር ቦታዎች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያ፣ የጉራጌ፣ የሰገን ህዝቦች፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ከፋ እና ቤንች ማጂ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም በጥቂት ቦታዎችም ላይ ደግሞ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም ይችላል። በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ይቆያል።</u>

## እ.ኤ.አ. ከማርች 11-20/2019 የሚኖረው  የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ ከማርች ሁለተኛው አስር ቀናት አጋማሽ በኋላ በአብዛኛው የበልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ በተለይም የደቡብና የመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች በመጠንም ሆነ በቦታ የተሻለ እርጥበት የሚያገኙበት ወቅት ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሀ አቅርቦት በጎ አስተዋጽኦ የሚያበረክትበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ አርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት የግጦሽና የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን ከማግኘት አንጻር የተሻለ ዕድል የሚያገኙበት ጊዜ ሲሆን፤ በሌላ መልኩ ከበልግ ወቅት ዝናብ ባህሪ አኳያ ደረቅ ሰሞናት የሚስተዋልበት ጊዜም ነው፡፡

በተሰጠው ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የማርች ሁለተኛው አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው ቀስ በቀስ እንደሚጠናከርና በአንዳንድ የበልግ ዝናብ አብቃይና ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለግብርና እንቅስቃሴ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ በተለየም ቀደም ብለው ለተዘሩ የአጭር ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ገንቢ ሚና የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የማሳ ዝግጅት ለማድረግ አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማጠራቀም የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ስለሚጠበቅ አርሶ አደሮችም ሆኑ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ እንመክራለን፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ኪስ ቦታዎች ላይ ከሚጠበቀው በጣም እርጥበታማ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ቀድመው የተዘሩ ሰብሎችና ለዘር የተዘጋጁ ማሳዎች በጎርፍ እንዳይጠረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ የሚገባ ቢሆንም፤ በመካከል ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ውኃን የመሰብሰብና የማጠራቀም ተግባራት ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል እርጥበት አጠርና ከፍተኛ የውኃ ትነት ያለባቸው አካባቢዎች የውኃን ብክነትን ለመከላከል የሚያሰችሉ ዘዴዎችን ሊተገብሩ ይገባል፡፡

## እ.ኤ.አ ከማርች 11-20/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው ትንብያ መሰረት በሚቀጥሉት አስር ቀናት የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የሰሜን እና የመካከለኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በዚህ መሰረት አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤና ስምጥሸለቆ እንዲሁም የላይኛው አዋሽ፣ የአባይ ደቡባዊና ምስራቃዊ አጋማሽ እንዲሁም የላይኛው ተከዜ፣ ዋቢሸበሌና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል የላይኛውና መካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የባሮአኮቦ ደቡብዊ ክፍል፣ የታችኛው ተከዜ እና የሰሜና አባይ ተፋሰሶች በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎችም ላይ ደግሞ ከባድ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ምንም እንኳን የበልግ ዝናብ ለወራጅ ውሃ ያለው አስተዋፆ አነስተኛ ቢሆንም፤ ከላይ በተጠቀሱት ተፋሰሶች ላይ የሚገኘው ዝናብ የከባቢ አየርን በማቀዝቀዝና በተወሰነ መጠን በአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲኖር አስተዋፆ ያደርጋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለገፀምድርና ለከርሰምድር ውሃ ሀብት ዘርፍ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡